## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩፡ አንተም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ የተሳለን ፡
ጐራዴ ፡ ውሰድ ፡ እንደ ፡ ጢም ፡ መላጫ ፡ ወደ ፡
አንተ ፡ ትወስደዋለህ ፡ ራስህንና ፡ ጢምህንም ፡
ትላጭበታለህ ፡ ሚዛንንም ፡ ውሰድ ፡ ጠጕሩ
፪፡ ንም ፡ ትከፋፍላለህ ። የመከበብም ፡ ወራት ፡
በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በከተማይቱ ፡ መካከል ፡ ሢሶ
ውን ፡ በእሳት ፡ ታቃጥላለህ ፡ ሢሶውንም ፡ ወስ
ደህ ፡ ዙሪያውን ፡ በጐራዴ ፡ ትመታለህ ፡ ሢሶ
ውንም ፡ ወደ ፡ ነፋስ ፡ ትበትናለህ ፡ እኔም ፡ በኋ
፫፡ ላቸው ፡ ጐራዴ ፡ እመዝዛለሁ ። ከዚያም ፡ በጥ
ቂቱ ፡ ውሰድ ፡ በመጐናጸፊያህም ፡ ጫፍ ፡ ቋጥ
፬፡ ራቸው ። ከእነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ወስደህ ፡ በእ
ሳት ፡ ውስጥ ፡ ትጥላለህ ፡ በእሳትም ፡ ታቃጥላ
ቸዋለህ ፡ ከዚያም ፡ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ እሳት ፡ ትወጣለች ።
፭፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
ይህች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ናት ፡ በአሕዛብም ፡ መካ
ከል ፡ አድርጌአታለሁ ፡ አገሮችም ፡ በዙሪያዋ ፡
፮፡ አሉ ። እርስዋም ፡ ከአሕዛብ ፡ ይልቅ ፡ ፍርዴን ፡
በኃጢአት ፡ ለወጠች ፡ በዙሪያዋም ፡ ካሉ ፡ አገ
ሮች ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ትእዛዜን ፡ ተላለፈች ፡
ፍርዴን ፡ ጥለዋልና ፡ በትእዛዜም ፡ አልሄዱ
፯፡ ምና ። ስለዚህ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡— በዙሪያችሁ ፡ ካሉት ፡ አሕዛብ ፡ ሰበብ ፡
ሆናችኋልና ፡ በትእዛዜም ፡ አልሄዳችሁምና ፡
ፍርዴንም ፡ አልጠበቃችሁምና ፡ በዙሪያች
ሁም ፡ እንዳሉ ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ፍርድ ፡ እንኳ ፡
፰፡ አላደረጋችሁምና ፡ ስለዚህ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እነሆ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡
በአንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፡ አሕዛብም ፡ እያዩ ፡ ፍር
፱፡ ድን ፡ በመካከልሽ ፡ አደርጋለሁ ። ስለ ፡ ርኵሰት
ሽም ፡ ሁሉ ፡ ያልሠራሁትን ፡ እርሱንም ፡ የሚ
መስል ፡ ደግሞ ፡ የማልሠራውን ፡ ነገር ፡ እሠራ
፲፡ ብሻለሁ ። ስለዚህ ፡ በመካከልሽ ፡ አባቶች ፡ ልጆ
ቻቸውን ፡ ይበላሉ ፡ ልጆችም ፡ አባቶቻቸውን ፡
ይበላሉ ፤ ፍርድንም ፡ አደርግብሻለሁ ፡ ከአን
ቺም ፡ የቀረውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ነፋሳት ፡ ሁሉ ፡
፲፩፡ እበትናለሁ ። ስለዚህ ፡ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡
በእድፍሽና ፡ በርኵሰትሽ ፡ መቅደሴን ፡ ስላረከ
ስሽ ፡ ስለዚህ ፡ በእውነት ፡ እኔ ፡ እሳንስሻለሁ ፡
ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓይኔም ፡ አይራ
፲፪፡ ራም ፡ እኔም ፡ አላዝንም ። ከአንቺም ፡ ሢሶው ፡
በቸነፈር ፡ ይሞታል ፡ በመካከልሽም ፡ በራብ ፡
ያልቃል ፤ ሢሶውም ፡ በዙሪያሽ ፡ በሰይፍ ፡ ይወ
ድቃል ፡ ሢሶውንም ፡ ወደ ፡ ነፋሳት ፡ ሁሉ ፡ እበ
ትናለሁ ፡ በኋላቸውም ፡ ሰይፍ ፡ እመዝዛለሁ ።
፲፫፡ ቍጣዬም ፡ ይፈጸማል ፡ መዓቴንም ፡ እጨር
ሳለሁ ፡ እጽናናማለሁ ፡ መዓቴንም ፡ በፈጸምሁ
በቸው ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅንዓቴ ፡
፲፬፡ እንደ ፡ ተናገርሁ ፡ ያውቃሉ ። በዙሪያሽም ፡
ባሉ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ በሚያልፉም ፡ ሁሉ ፡
ፊት ፡ በድማና ፡ መሰደቢያ ፡ አደርግሻለሁ ።
በቍጣና ፡ በመዓት ፡ በመዓትም ፡ ሀለፋ ፡ ፍር ፲፭፡
ድን ፡ ባደረግሁብሽ ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያሽ ፡ ላሉ ፡
አሕዛብ ፡ መሰደቢያና ፡ መተረቻ ፡ ተግሣጽና ፡
መደነቂያ ፡ ይሆናል ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡
ተናግሬአለሁ ። ለማጥፋትም ፡ የሆነውን ፡ ፲፮፡
አጠፋችሁም ፡ ዘንድ ፡ የምሰድደውን ፡ የራብ ፡
ፍላጻ ፡ በላያችሁ ፡ በሰደድሁ ፡ ጊዜ ፡ ራብን ፡
አብዛምርባችኋለሁ ፡ የእንጀራችሁንም ፡ በትር ፡
እሰብራለሁ ። ራብንና ፡ ክፉዎችን ፡ አራዊት ፡ ፲፯፡
እሰድድባችኋለሁ ፡ ልጆቻችሁንም ፡ ያጠፉሉ ፡
ቸነፈርና ፡ ደምም ፡ በአንቺ ፡ ዘንድ ፡ ያልፋሉ ፡
ሰይፍንም ፡ አመጣብሻለሁ ። እኔ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ይህን ፡ ተናግሬአለሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እን ፩፡
ዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ፪፡
ፊትህን ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ተራሮች ፡ አቅና ፡
ትንቢትም ፡ ተናገርባቸው ። እንዲህም ፡ በል ፡— ፫፡
የእስራኤል ፡ ተራሮች ፡ ሆይ ፡ የጌታን ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡
ለተራሮችና ፡ ለኮረብቶች ፡ ለምንጮችና ፡
ለሸለቆች ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— እኔ ፡ እነሆ ፡
እኔ ፡ ሰይፍን ፡ አመጣባችኋለሁ ፡ የኮረብታው ፡
መስገጃዎቻችሁንም ፡ አጠፋለሁ ። መሠዊያ ፬፡
ዎቻችሁም ፡ ይፈርሳሉ ፡ የፀሐይም ፡ ምስሎቻ
ችሁ ፡ ይሰበራሉ ፡ ተወግተውም ፡ የሞቱትን ፡
ሰዎቻችሁን ፡ በጣዖቶቻችሁ ፡ ፊት ፡ እጥላለሁ ።
የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ሬሳዎች ፡ በጣዖቶቻ ፭፡
ቸው ፡ ፊት ፡ አኖራለሁ ፡ አጥንቶቻችሁንም ፡
በመሠዊያዎቻችሁ ፡ ዙሪያ ፡ እበትናለሁ ። በም ፮፡
ትኖሩበትም ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ከተሞቹ ፡ ይፈር
ሳሉ ፡ የኮረብታው ፡ መስገጃዎችም ፡ ሁሉ ፡
ውድማ ፡ ይሆናሉ ፡ መሠዊያዎቻችሁም ፡ ይፈ
ርሳሉ ፡ በድማም ፡ ይሆናሉ ፡ ጣዖቶቻችሁም ፡
ይሰበራሉ ፡ ያልቃሉም ፡ የፀሐይም ፡ ምስሎ
ቻችሁ ፡ ይቈረጣሉ ፡ ሥራችሁም ፡ ይሻራል ።
ተወግተውም ፡ የሞቱት ፡ በመካከላችሁ ፡ ይወ ፯፡
ድቃሉ ፡ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡
ታውቃላችሁ ።
ነገር ፡ ግን ፡ በአገሮች ፡ በተበተናችሁ ፡ ጊዜ ፡ ፰፡
ከሰይፍ ፡ ያመለጡትን ፡ ቅሬታ ፡ በአሕዛብ ፡
መካከል ፡ አስቀርላችኋለሁ ። ከእናንተም ፡ ፱፡
የዳኑት ፡ ከእኔ ፡ በራቀው ፡ በአመንዝራ ፡ ልባ
ቸውና ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡ በተከተሉ ፡ በአመን
ዝራ ፡ ዓይኖቻቸው ፡ የተሰበርሁትን ፡ እኔን ፡
ወደ ፡ እነርሱ ፡ በተማረኩት ፡ አሕዛብ ፡ መካ
ከል ፡ ሆነው ፡ ያስቡኛል ፤ በርኵሰታቸውም ፡
ሁሉ ፡ ስላደረጉት ፡ ክፋት ፡ ራሳቸውን ፡ ይጸየ
ፋሉ ። እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ፲፡
ያውቃሉ ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደርግባቸው ፡
ዘንድ ፡ መናገሬ ፡ በከንቱ ፡ አይደለም ።
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— በእ ፲፩፡
ጅህ ፡ አጨብጭብ ፡ በእግርህም ፡ አሸብሽብ ፡



እንዲህም ፡ በል ፡— በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈ
ርም ፡ ይወድቃሉና ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ቤት ፡
ስለ ፡ አስጸያፊ ፡ ሥራዎቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ወዮ !
፲፪፡ በሩቅ ፡ ያለው ፡ በቸነፈር ፡ ይሞታል ፡ በቅር
ብም ፡ ያለው ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃል ፡ የቀረ
ውና ፡ የዳነውም ፡ በራብ ፡ ይሞታል ፤ እንዲሁ ፡
፲፫፡ መዓቴን ፡ እፈጽምባቸዋለሁ ። ተወግተውም ፡
የሞቱ ፡ ሰዎቻቸው ፡ በጣዖቶቻቸው ፡ መካከልና ፡
በመሠዊያዎቻቸው ፡ ዙሪያ ፡ ለጣዖቶቻቸው ፡
ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ በቀረቡበት ፡ ስፍራ ፡ ከፍ ፡
ባለው ፡ ኮረብታ ፡ ሁሉ ፡ በተራሮችም ፡ ራስ ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ከለመለመውም ፡ ዛፍ ፡ ሁሉ ፡
በታች ፡ ቅጠሉም ፡ ከበዛ ፡ ከአድባር ፡ ዛፍ ፡
ሁሉ ፡ በታች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብ
፲፬፡ ሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ታውቃላችሁ ። እጄንም ፡
እዘረጋባቸዋለሁ ፡ በሚኖሩበትም ፡ ስፍራ ፡
ሁሉ ፡ ምድሪቱን ፡ ከዴብላታ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ይልቅ ፡ ውድማና ፡ በረሀ ፡ አደርጋታለሁ ፡ እኔም ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ያውቃሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እን
፪፡ ዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡
ሆይ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ምድር ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡— ፍጻሜ ፡ በምድሪቱ ፡ በአ
፫፡ ራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ላይ ፡ ፍጻሜ ፡ ደርሶአል ። አሁን ፡
ፍጻሜ ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ቍጣዬንም ፡
እሰድድብሻለሁ ፡ እንደ ፡ መንገድሽም ፡ መጠን ፡
እፈርድብሻለሁ ፡ ኵስቍልናሽንም ፡ ሁሉ ፡
፬፡ አመጣብሻለሁ ። ዓይኔም ፡ አይራራልሽም ፡
እኔም ፡ አላዝንም ፤ መንገድሽንም ፡ አመጣብሻ
ለሁ ፡ ርኵሰትሽም ፡ በመካከልሽ ፡ ይሆናል ፡
እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ታው
ቃላችሁ ።
፭፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
ክፉ ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እነሆ ፡ ይመ
፮፡ ጣል ። ፍጻሜ ፡ መጥቶአል ፡ ፍጻሜ ፡ መጥቶ
፯፡ አል ፡ ነቅቶብሻል ፤ እነሆ ፡ ደርሶአል ። በም
ድር ፡ የምትቀመጥ ፡ ሆይ ፡ ተራህ ፡ ደርሶአል ፡
ጊዜ ፡ መጥቶአል ፡ ቀን ፡ ቀርቦአል ፤ የሽብር ፡
ቀን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ እልልታ ፡
፰፡ አይደለም ። አሁን ፡ በቅርብ ፡ መዓቴን ፡ አፈስ
ስብሻለሁ ፡ ቍጣዬንም ፡ እፈጽምብሻለሁ ፡
እንደ ፡ መንገድሽም ፡ መጠን ፡ እፈርድብሻለሁ ፡
፱፡ ኵስቍልናሽንም ፡ ሁሉ ፡ አመጣብሻለሁ ። ዓይ
ኔም ፡ አይራራም ፡ እኔም ፡ አላዝንም ፤ እንደ ፡
መንገድሽም ፡ መጠን ፡ አመጣብሻለሁ ፡ ርኵሰ
ትሽም ፡ በመካከልሽ ፡ ይሆናል ፡ እኔም ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ የምቀሥፍ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ታው
ቃላችሁ ።
፲፡ እነሆ ፡ ቀኑ ፡ እነሆ ፡ መጥቶአል ፤ ተራህ ፡
ወጥቶአል ፤ ብትር ፡ አብቦአል ፡ ትዕቢትም ፡
፲፩፡ አቈብቍሎአል ። ግፍ ፡ ወደ ፡ ክፋት ፡ ብትር ፡
ተነሥቶአል ፤ ከእነርሱና ፡ ከብዛታቸው ፡ ከሀብ
ታቸውም ፡ ምንም ፡ አይቀርም ፡ የሚያለቅስላ
ቸውም ፡ የለም ። ጊዜው ፡ መጥቶአል ፡ ቀኑ ፡ ፲፪፡
ቀርቦአል ፤ መዓት ፡ በብዙዎች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ነውና ፡ የሚገዛ ፡ ደስ ፡ አይበለው ፡ የሚሸጥም ፡
አያልቅስ ። የሚሸጥ ፡ ወደ ፡ ሸጠው ፡ ነገር ፡ ፲፫፡
አይመለስም ፡ ሰውም ፡ በነፍሱ ፡ ኃጢአት ፡
አይጸናም ።
መለከቱን ፡ ነፍተዋል ፡ ሁሉንም ፡ አዘጋጅተ ፲፬፡
ዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መዓቴ ፡ በብዙዎች ፡ ሁሉ ፡
ላይ ፡ ነውና ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚሄድ ፡ የለም ።
ሰይፍ ፡ በውጭ ፡ ቸነፈርና ፡ ራብ ፡ በውስጥ ፡ አለ ፤ ፲፭፡
በሜዳ ፡ ያለው ፡ በሰይፍ ፡ ይሞታል ፡ በከተ
ማም ፡ ያለውን ፡ ቸነፈርና ፡ ራብ ፡ ይፈጁታል ።
ከእነርሱም ፡ የሚሸሹ ፡ ይድናሉ ፡ በተራራም ፡ ፲፮፡
ላይ ፡ ይሆናሉ ፤ እኔም ፡ በኃጢአታቸው ፡ ሁሉን ፡
እገድላለሁ ። እጅ ፡ ሁሉ ፡ ትደከማለች ፡ ጕልበ ፲፯፡
ትም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ ትቀልጣለች ። ማቅም ፡ ፲፰፡
ይለብሳሉ ፡ ድንጋጤም ፡ ይሸፍናቸዋል ፤ በፊ
ትም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እፍረት ፡ ይሆናል ፡ ራሳቸ
ውንም ፡ ሁሉ ፡ ይነጩታል ። ብራቸውን ፡ በጎ ፲፱፡
ዳናዎቹ ፡ ላይ ፡ ይጥላሉ ፡ ወርቃቸውም ፡ እንደ ፡
ጕድፍ ፡ ይሆናል ፤ በእግዚአብሔር ፡ መዓት ፡
ቀን ፡ ብራቸውና ፡ ወርቃቸው ፡ ያድናቸው ፡
ዘንድ ፡ አይችልም ። እርሱ ፡ የኃጢአታቸው ፡
ዕንቅፋት ፡ ሆኖአልና ፡ ሰውነታቸውን ፡ አያጠግ
ቡም ፡ ሆዳቸውንም ፡ አይሞሉም ። የክብሩንም ፡ ፳፡
ጌጥ ፡ ወደ ፡ ትዕቢት ፡ ለወጡ ፡ የርኵስነታቸ
ውንም ፡ ምስሎች ፡ አደረጉበት ፤ ስለዚህ ፡ እኔ ፡
በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ አድርጌአታለሁ ።
በባዕድም ፡ እጅ ፡ ለንጥቂያ ፡ በምድር ፡ ኃጢአ ፳፩፡
ተኞችም ፡ እጅ ፡ ለብዝበዛ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣታ
ለሁ ፤ እነርሱም ፡ ያረክሱአታል ። ፊቴን ፡ ከእ ፳፪፡
ነርሱ ፡ ዘንድ ፡ እመልሳለሁ ፡ ምሥጢሬንም ፡
ያረክሳሉ ፤ ወንበዴዎችም ፡ ይገቡበታል ፡ ያረ
ክሱአትማል ።
ምድር ፡ ደም ፡ በመጣው ፡ በደል ፡ ከተማም ፡ ፳፫፡
በግፍ ፡ ተሞልታለችና ፡ ሰንሰለት ፡ ሥራ ። ከአ ፳፬፡
ሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ከሁሉ ፡ የሚከፉትን ፡ አመጣ
ለሁ ፡ ቤቶቻቸውንም ፡ ይወርሳሉ ፤ የኃያላን
ንም ፡ ትዕቢት ፡ አጠፋለሁ ፡ መቅደሶቻቸውም ፡
ይረክሳሉ ። ጥፋት ፡ መጥቶአል ፤ ሰላምም ፡ ፳፭፡
ይሻሉ ፡ እርሱም ፡ አይገኝም ። ድንጋጤ ፡ በድ ፳፮፡
ንጋጤ ፡ ላይ ፡ ይመጣል ፡ ወሬም ፡ ወሬውን ፡
ይከተላል ፡ ከነቢዩም ፡ ዘንድ ፡ ራእይን ፡ ይሻሉ ፤
ከካህኑም ፡ ዘንድ ፡ ትምህርት ፡ ከሽማግሌዎ
ችም ፡ ዘንድ ፡ ምክር ፡ ይጠፋል ። ንጉሡም ፡ ያለ ፳፯፡
ቅሳል ፡ አለቃም ፡ ውርደትን ፡ ይለብሳል ፡ የም
ድርም ፡ ሕዝብ ፡ እጅ ፡ ትንቀጠቀጣለች ፤ እንደ ፡
መንገዳቸውም ፡ መጠን ፡ አደርግባቸዋለሁ ፡
በፍርዳቸውም ፡ መጠን ፡ እፈርድባቸዋለሁ ፤
እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ያው
ቃሉ ።

፲፱፡ ነገር፡ግን፡በግብጽ፡ምድር፡የገለሞተችበትን፡
የኰረዳነትዋን ፡ ዘመን ፡ አስባ ፡ ግልሙትና
፳፡ ዋን፡አበዛች ። ሥጋቸውም፡እንደ፡አህዮች፡
ሥጋ፡ዘራቸውም፡እንደ፡ፈረሶች ፡ ዘር ፡ የሆ
ነውን፡እነዚያን፡ምልምሎች ፡ በፍቅር ፡ ተከ
፳፩፡ ተለቻቸው ። ስለ፡ኰረዳነትሽ፡ምክንያት፡ግብ
ጻውያን፡ጡቶችሽን፡በዳበሱ፡ ጊዜ ፡ የኰረዳ
ነትሽን፡ሴሰኝነት፡አሰብሽ ።
፳፪፡ ስለዚህ ÷ አሖሊባ ፡ ሆይ ÷ ጌታ ፡ እግዚአብ
ሔር፡እንዲህ፡ይላል ፡— ነፍስሽ፡ከእነርሱ፡የተ
ለየች ፡ ውሽሞችሽን፡አስነሣብሻለሁ ÷ በዙርያ
፳፫፡ ሽም ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡ አመጣቸዋለሁ ። እነር
ሱም፡የባቢሎን፡ሰዎች፡ከለዳውያንም፡ሁሉ÷
ፋቁድ ÷ ሱሔ ÷ ቆዓ ÷ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ አሦ
ራውያን፡ሁሉ ÷ መልከ ፡ መልካሞች ፡ ጐበዛ
ዝት ÷ አለቆችና ፡ ሹማምቶች ፡ ሁሉ ÷ መሳፍ
ንቶችና ፡ አማካሪዎች ፡ ሁሉ ÷ በፈረስ ፡ ላይ ፡
፳፬፡ የተቀመጡ ፡ ናቸው ። በሠረገላና ፡ በሰረገላ ፡
በመንኰራኵርም ፡ በአሕዛብም ፡ ጉባኤ ፡ ይመ
ጡብሻል ፤ ጋሻና ፡ አላባሽ ፡ ጋሻ ፡ ራስ ፡ ቍርም ፡
ይዘው ፡ በዙሪያሽ ፡ ይዘጋጁብሻል ፤ ፍርድ
ንም ፡ እሰጣቸዋለሁ ÷ እንደ ፡ ፍርዳቸውም ፡
፳፭፡ ይፈርዱብሻል ። ቅንዓቴንም ፡ በአንቺ ፡ ላይ ፡
አደርጋለሁ ፡ በመዓትም ፡ ያደርጉብሻል ፡ አፍ
ንጫሽንና ፡ ጆሮሽንም ፡ ከአንቺ ፡ ይቈርጣሉ ÷
ከአንቺም ፡ የቀረ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃል ፤
ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችሽንም ፡ ማርከው ፡
ይወስዳሉ ÷ ከአንቺም ፡ የቀረውን ፡ እሳት ፡ ትብ
፳፮፡ ላቸዋለች ። ልብስሽንም ፡ ይገፍፉሻል ፡ የክብ
፳፯፡ ርሽንም ፡ ጌጥ ፡ ይወስዳሉ ። ሴሰኝነትሽንም ÷
ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣሽውን ፡ ግልሙትናሽ
ንም ፡ ከአንቺ ፡ አስቀራለሁ ፡ ዓይንሽንም ፡ ወደ ፡
እነርሱ ፡ አታነሺም ፡ ግብጽንም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡
፳፰፡ አታስቢም ። ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላልና ፡— እነሆ ÷ በጠላሻቸው ፡ እጅ ÷ ነፍ
ስሽ ፡ በተለየቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥ
፳፱፡ ሻለሁ ፡ እነርሱም ፡ በጥል ፡ ያደርጉብሻል ÷
የደከምሽበትንም ፡ ሁሉ ፡ ይወስዳሉ ÷ ዕራቁት
ሽንና ፡ ዕርቃንሽን ፡ አድርገውም ፡ ይተዉሻል ፤
የግልሙትናሽም ፡ ነውር ÷ ሴሰኝነትሽና ፡ ግል
፴፡ ሙትናሽም ፡ ሁሉ ፡ ይገለጣል ። ከአሕዛብ ፡ ጋር ፡
ስላመነዘርሽ ፡ በጣዖቶቻቸውም ፡ ስለ ፡ ረከስሽ ፡
፴፩፡ ይህን ፡ ያደርጉብሻል ። በእኅትሽ ፡ መንገድ ፡
ሄደሻል ፡ ስለዚህ ፡ ጽዋዋን ፡ በእጅሽ ፡ እሰጥሻ
፴፪፡ ለሁ ። ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
የጠለቀውንና ፡ የሰፋውን ፡ ብዙም ፡ የሚይዘ
ውን ፡ የእኅትሽን ፡ ጽዋ ፡ ትጠጪአለሽ ፡ መሳ
፴፫፡ ቂያና ፡ መሳለቂያም ፡ ትሆኛለሽ ። በእኅትሽ ፡
በሰማርያ ፡ ጽዋ ÷ በድንጋጤና ፡ በጥፋት ፡ ጽዋ ÷
፴፬፡ በስካርና ፡ በውርደት ፡ ትሞያለሽ ። ትጠጪ
ዋለሽ ፡ ትጨልጪውማለሽ ፡ ገሉንም ፡ ታኝኪ
ዋለሽ ፡ ጡትሽንም ፡ ትሸነትሪዋለሽ ፤ እኔ ፡ ተና
፴፭፡ ግሬአለሁና ÷ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ስለዚህ ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ዘንግ
ተሽኛልና ÷ ወደ ፡ ኋላሽም ፡ ጥለሽኛልና ፡
አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ሴሰኝነትሽንና ፡ ግልሙትና
ሽን ፡ ተሸከሚ ።
እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡— የሰው ፡ ፴፮፡
ልጅ ፡ ሆይ ÷ በአሖላና ፡ በአሖሊባ ፡ ትፈርዳለ
ህን ? ኃጢአታቸውንም ፡ ታስታውቃቸዋለህን ?
አመንዝረዋልና ÷ ደምም ፡ በእጃቸው ፡ አለና ÷ ፴፯፡
ከጣዖቶቻቸውም ፡ ጋር ፡ አመንዝረዋልና ÷ ለእ
ኔም ፡ የወለዱአቸውን ፡ ልጆቻቸውን ፡ መብል ፡
እንዲሆኑላቸው ፡ በእሳት ፡ አሳልፈዋቸዋልና ።
ይህን ፡ ደግሞ ፡ አድርገውብኛል ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ፴፰፡
መቅደሴን ፡ አርክሰዋል ፡ ሰንበታቴንም ፡ ሽረ
ዋል ። ልጆቻቸውንም ፡ ለጣዖቶቻቸው ፡ በሠዉ ፡ ፴፱፡
ጊዜ ÷ በዚያው ፡ ቀን ፡ ያረክሱት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
መቅደሴ ፡ ገቡ ፤ እነሆም ÷ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ እን
ደዚህ ፡ አደረጉ ። ደግሞ ፡ መልእክተኛ ፡ ወደ ፡ ፵፡
ተላከባቸው ፡ ከሩቅም ፡ ወደሚመጡ ፡ ሰዎች ፡
ልካችኋል ፤ እነሆም ፡ መጡ ÷ አንቺም ፡ ታጠ
ብሽላቸው ፡ ዓይኖችሽንም ፡ ተኳልሽ ፡ ጌጥም ፡
አጌጥሽ ፡ በክብር ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ተቀመጥሽ ÷ ፵፩፡
በፊት ፡ ለፊትዋም ፡ ማዕድ ፡ ተዘጋጅታ ፡ ነበር ÷
ዕጣኔንና ፡ ዘይቴንም ፡ አኖርሽበት ። የደስተኞ ፵፪፡
ችም ፡ ድምፅ ፡ በእርስዋ ፡ ዘንድ ፡ ነበረ ፤ ከብ
ዙም ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ ጋር ፡ ሰካራሞቹ ፡ ከም
ድረ ፡ በዳ ፡ መጡ ፤ በእጃቸው ፡ አንባር ፡ በራሳ
ቸውም ፡ የተዋበ ፡ አክሊል ፡ አደረጉ ። እኔም ፡ ፵፫፡
በምንዝር ፡ ላረጀችው ፡— አሁን ፡ ከእርስዋ ፡
ጋር ፡ ያመነዝራሉ ፡ እርስዋም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡
ታመነዝራለች ፡ አልሁ ። ወደ ፡ ጋለሞታም ፡ ፵፬፡
እንደሚገቡ ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ ገቡ ፤ እንዲሁ ፡
ይሰስኑ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አሖላና ፡ ወደ ፡ አሖሊባ ፡
ገቡ ። ሴቶቹ ፡ አመንዝሮች ፡ ናቸውና ÷ በእ ፵፭፡
ጃቸውም ፡ ደም ፡ አለና ፡ ጻድቃን ፡ ሰዎች ፡
በአመንዝሮቹና ፡ በደም ፡ አፍሳሾቹ ፡ ሴቶች ፡
ላይ ፡ በሚፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ይፈርዱባቸዋል ።
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ፵፮፡
ጉባኤን ፡ አመጣባቸዋለሁ ÷ ለመበተንና ፡ ለመ
በዝበዝም ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለሁ ። ጉባኤ ፵፯፡
ውም ፡ በድንጋይ ፡ ይወግሩአቸዋል ፡ በሰይፋቸ
ውም ፡ ይቈርጡአቸዋል ÷ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡
ልጆቻቸውንም ፡ ይገድላሉ ÷ ቤቶቻቸውንም ፡
በእሳት ፡ ያቃጥላሉ ። ሴቶችም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ፵፰፡
ሴሰኝነታችሁ ፡ እንዳይሠሩ ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፡
ሴሰኝነትን ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አጠፋለሁ ። ሴሰ ፵፱፡
ኝነታችሁንም ፡ በላያችሁ ፡ ላይ ፡ ይመልሳሉ ÷
እናንተም ፡ የጣዖቶቻችሁን ፡ ኃጢአት ፡ ትሸ
ከማላችሁ ፡ እኔም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡
ሆንሁ ፡ ታውቃላችሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በአሥረኛው ፡ ወር ፡ ፩፡
ከወሩም ፡ በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፡— የሰው ፡ ፪፡
ልጅ ፡ ሆይ ÷ የዚህን ፡ ቀን ÷ የዛሬን ፡ ቀን ፡ ስም ፡



ጻፍ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡
፫፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቀረበ ። ለዓመፀኛውም ፡ ቤት ፡
ምሳሌን ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በላቸው ፡—
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ጣድ ÷
ምንቸቱን ፡ ጣድ ÷ ውኃም ፡ ጨምርበት ።
፬፡ ቍራጮዋንም ÷ መልካሙን ፡ ቍራጭ ፡ ሁሉ ÷
ጭኑንና ፡ ወርቹን ፡ በእርስዋ ፡ ውስጥ ፡ ሰብስብ ÷
፭፡ የተመረጡትንም ፡ አጥንቶች ፡ ሙላበት ። ከመ
ንጋው ፡ የተመረጠውን ፡ ውሰድ ÷ አጥንቶ
ቹም ፡ እንዲበስሉ ፡ እንጨት ፡ በበታችዋ ፡
ማገድ ፤ አጥንቶቹም ፡ በውስጥዋ ፡ ይቀቀሉ ።
፮፡ ስለዚህ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡— ዝገትዋ ፡ ላለባት ፡ ዝገትዋም ፡ ከእር
ስዋ ፡ ላልወጣ ፡ ምንቸት ÷ ለደም ፡ ከተማ ፡
ወዮላት ! ቍራጭ ፡ ቍራጩን ፡ አውጣ ፡ ዕጣ ፡
፯፡ አልወደቀበትም ። ደምዋ ፡ በውስጥዋ ፡ አለ ።
በተራቈተ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አደረገችው ፡ እንጂ ፡
በአፈር ፡ ይከደን ፡ ዘንድ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ አላ
፰፡ ፈሰሰችውም ፡ መዓቴን ፡ አወጣ ፡ ዘንድ ÷ በቀ
ሌንም ፡ እበቀል ፡ ዘንድ ÷ ደምዋ ፡ እንዳይከደን ፡
፱፡ በተራቈተ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አደረግሁ ። ስለዚህ ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ለደም ፡
ከተማ ፡ ወዮላት ! እኔ ፡ ደግሞ ፡ ማገዶዋን ፡
፲፡ ታላቅ ፡ አደርገዋለሁ ። እንጨቱን ፡ አብዛ ፡
እሳቱን ፡ አንድድ ፤ ሥጋውን ፡ ቀቅል ፡ መረ
ቁን ፡ አጣፍጠው ፤ አጥንቶቹ ፡ ይቃጠሉ ።
፲፩፡ ትሞቅም ፡ ዘንድ ፡ ናስዋም ፡ ትግል ፡ ዘንድ ፡
ርኵስትዋም ፡ በውስጥዋ ፡ ይቀልጥ ፡ ዘንድ ፡
ዝገትዋም ፡ ይጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ባዶዋን ፡ በፍም ፡
፲፪፡ ላይ ፡ አድርጋት ። በከንቱ ፡ ደከመች ፡ ሆኖም ፡
፲፫፡ ዝገትዋ ፡ በእሳት ፡ ስንኳ ፡ አልለቀቀም ። በርኵ
ሰትሽ ፡ ሴሰኝነት ፡ አለ ፡ አነጻሁሽ ፡ አልነጻ
ሽምና ፡ መዓቴን ፡ በላይሽ ፡ እስክጨርስ ፡
ድረስ ፡ እንግዲህ ፡ ከርኵሰትሽ ፡ አትነጺም ።
፲፬፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬአለሁ ፡ ይመጣል ÷
እኔም ፡ አደርገዋለሁ ፤ አልመለስም ÷ አልራ
ራም ÷ አልጸጸትም ፡ እንደ ፡ መንገድሽና ፡ እንደ ፡
ሥራሽ ፡ ይፈርዱብሻል ÷ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚ
አብሔር ።
፲፭፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡
፲፮፡ ሲል ፡ መጣ ፡— የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ እነሆ ÷
የዓይንህን ፡ አምሮት ፡ በመቅሠፍት ፡ እወስድ
ብሃለሁ ፡ አንተም ፡ ወዮ ፡ አትበል ፡ አታልቅስም ፡
፲፯፡ እንባህንም ፡ አትፍሰስ ። በቀስታ ፡ ተክዝ ፤
ለሞዋቾችም ፡ አታልቅስ ÷ መጠምጠሚያህን ፡
በራስህ ፡ ላይ ፡ አድርግ ÷ ጫማህንም ፡ በእግ
ርህ ፡ አጥልቅ ÷ ከንፈሮችህንም ፡ አትሸፍን ፡
፲፰፡ የሰዎችንም ፡ እንጀራ ፡ አትብላ ። እኔም ፡ በማ
ለዳ ፡ ለሕዝቡ ፡ ተናገርሁ ÷ ወደ ፡ ማታም ፡ ሚስቴ ፡
ሞተች ፤ በነጋውም ፡ እንደ ፡ ታዘዝሁ ፡ አደረ
ግሁ ።
፲፱፡ ሕዝቡም ፡— ይህ ፡ የምታደርገው ፡ ነገር ፡
ለእኛ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አትነግረንምን ?
፳፡ አሉኝ ። እኔም ፡ እንዲህ ፡ አልኋቸው ፡— የእ
ግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
መጣ ፡— ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ተናገር ፡ እንዲ ፳፩፡
ህም ፡ በል ፡— ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፡— እነሆ ÷ የኃይላችሁን ፡ ትምክሕት ÷
የዓይናችሁን ፡ አምሮት ÷ የነፍሳችሁን ፡ ምኞት ፡
መቅደሴን ፡ አረክሳለሁ ፡ ያስቀራችኋቸውም ፡
ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችሁ ፡ በሰይፍ ፡ ይወ
ድቃሉ ። እኔም ፡ እንዳደረግሁ ፡ እናንተ ፡ ታደ ፳፪፡
ርጋላችሁ ፤ ከንፈራችሁን ፡ አትሸፍኑም ፡ የሰዎ
ችንም ፡ እንጀራ ፡ አትበሉም ። መጠምጠሚ ፳፫፡
ያችሁም ፡ በራሳችሁ ፡ ጫማችሁም ፡ በእግራ
ችሁ ፡ ይሆናል ፤ ዋይ ፡ አትሉም ፡ አታለቅሱ
ምም ፡ በኃጢአታችሁም ፡ ትሰለስላላችሁ ÷
እርስ ፡ በርሳችሁም ፡ ታንጐራጕራላችሁ ። ሕዝቅ ፳፬፡
ኤልም ፡ ምልክት ፡ ይሆናችኋል ፤ እርሱ ፡ እንዳ
ደረገ ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ ታደርጋላችሁ ፡ ይህም ፡
በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡
ሆንሁ ፡ ታውቃላችሁ ።
አንተም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ ኃይላቸውን ÷ ፳፭፡
የተመኩበትንም ፡ ደስታ ÷ የዓይናቸውን ፡ አም
ሮት ÷ የነፍሳቸውንም ፡ ምኞት ÷ ወንዶችና ፡
ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ በወሰድሁባቸው ፡ ቀን ÷
በዚያ ፡ ቀን ፡ ያመለጠው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በጆ ፳፮፡
ሮህ ፡ ያሰማ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ይመጣል ።
በዚያ ፡ ቀን ፡ አፍህ ፡ ላመለጠው ፡ ይከፈታል ÷ ፳፯፡
አንተም ፡ ትናገራለህ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ዲዳ ፡
አትሆንም ፤ ምልክትም ፡ ትሆናቸዋለህ ÷ እኔም ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ያውቃሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፭ ።

የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ፩፡
ሲል ፡ መጣ ፡— የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ ፊትህን ፡ ፪፡
ወደ ፡ አሞን ፡ ልጆች ፡ አቅንተህ ፡ ትንቢት ፡
ተናገርባቸው ። ለአሞንም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ፫፡
በል ፡— የጌታን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስሙ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—
መቅደሴ ፡ በረከሰ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤልም ፡ ምድር ፡
በድማ ፡ በሆነች ፡ ጊዜ ፡ የይሁዳም ፡ ቤት ፡ በተ
ማረኩ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ እሰይ ፡ ብለሃልና ፡
ስለዚህ ÷ እነሆ ÷ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ለምሥራቅ ፡ ፬፡
ልጆች ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥሃለሁ ÷ እነርሱም ፡
በአንተ ፡ ውስጥ ፡ ይሰፍራሉ ÷ ማደሪያዎቻቸ
ውንም ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ ይሠራሉ ፤ ፍሬህን ፡
ይበላሉ ፡ ወተትህንም ፡ ይጠጣሉ ። የአሞንን ፡ ፭፡
ከተማ ፡ ለግመሎች ፡ ማሰማርያ ÷ የአሞንንም ፡
ልጆች ፡ ለመንጋ ፡ መመሰጊያ ፡ አደርጋለሁ ፡
እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ታውቃ
ላችሁ ። ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላ ፮፡
ልና ፡— በእጅህ ፡ አጨብጭበሃልና ÷ በእግር
ህም ፡ አሸብሽበሃልና ÷ በእስራኤልም ፡ ምድር ፡
ላይ ፡ በነፍስህ ፡ ንቀት ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ብሎሃልና ፡
ስለዚህ ÷ እነሆ ÷ እጄን ፡ ዘርግቼብሃለሁ ÷ ለአ ፯፡
ሕዛብም ፡ አስበዘብዝሃለሁ ÷ ከአሕዛብም ፡
ለይቼ ፡ አቈርጥሃለሁ ÷ ከአገሮችም ፡ አጠፋሃ

